# በዘር ላይ ያተኮረ "ከፋፍለህ ግዛ"
# ፖሊሲ ማን ሊፈታልን ይችላልን?

ተስፋሁን ዘለንደን

October 3, 2018
2017  (2011 ዓ.ም.)

የአፍሪካ አኅጉር እንዲሁም ኢትዮጵያ ለዘመናት ለሚቀጥሉት ዘመናት ዓመታት በዘር (በጎሳ) ላይ የተመረኮዘ ፈተናዎች እንደሚጠብቃት ብዙዎች ይናገሩታል፡፡ ይህም ሲባል

1ኛ) በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በባርነት ሽያጭ፤

2ኛ) ከ18ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን የቅኝ ግዛት በአፍሪካ እና በ3ኛ ዓለም አገሮች ላይ ተንሰራፍተው ነበር፡፡

3ኛ) በአሁኑ ዘመን የተቀመረው እና የተቀነባበረው የ21ኛው ክፍለዘመን ፕሮግራም ከፋፍለህ ግዛው፤ (በሃይማኖት፣ በዘር (በጎሳ)፣ በቋንቋ ፊደል … በሌላም)

በዚህ በ3ኛው ቁጥር ላይ ያለው የብሔር ፓለቲካ በሕገ መንግሥት ተደርቶ ፤ የፓለቲካ ፕሮግራም ተቀርጾለትና ካድሬ ተቀጥሮለት የሚንቆለጳጰሰው። አውሮፓ የተማርን ነን ባሉት (የተማሪዎች ንቅናቄ) እና በጥቂት የትግራይ ልጆች እንዲሁም የኦሮሞ ልጆች፤ ጎሰኞች ከልጅነታቸው የተጋቱት የጥላቻ ፓለቲካና ስብከት ህሊናቸውን ጋርዶት ዛሬም ሚሊዮኖች በገዛ ሀገራቸው ለስደትና እንግልት የመበታተን ስቃይ የሀገሪቱ መዳኛ ነው ሲሉ ያደነቁሩናል። እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው ፡-

1) ከሶማሌ ክልል አዋሳኝ ግዛቶች እስከ 1.5 ሚሊዮን ኦሮሞዎች የተፈናቀሉት በጎሳ ፓለቲካ ርዕዮት መዘዝ ነው።

2) ጅግጅጋ 'መጤ' ተብለው ንጹሐን የታረዱት ዘር እየተለየ ንብረት የወደመው በጎሳ ፓለቲካ ሰበብ ነው።

3) ከ400 እስከ 500 ሺ የሚገመቱ የጌድኦ ተወላጆች ከቀያቸው የተፈናቀሉት በጎሳ ፓለቲካ መንስኤ ነው።

4) ቡራዮ ላይ በትንሹ ከ49 በላይ አብዛኛዎቹ የጋሞ ተወላጆች የተገደሉት ከ13ሺ በላይ ወገኖቻችን የተፈናቀሉት በጎሳ ፓለቲካ መንስኤነት ነው።

5) ዛሬም ከ70ሺ በላይ ወገኖቻችን ከቤኒሻንጉል ክልል የተፈናቀሉት በጥቂቱ 49 ንጹሀን የተገደሉት በጎሳ ፓለቲካ ሳቢያ ነው።

6) ከኦሮሚያ ክልል አማሮች የተፈናቀሉት ዘግናኝ በሆነ የጎሳ ፖለቲካ ነው [1]

እውነታው ይሄ ነው ፤ ምን ቢኳኳል አሳማ መልከጥፉነቱን እንደማይቀይር ሁሉ የጎሳ ፓለቲካም ልሂቃኑን ወደ ስልጣን ማማ ከማድረስ ውጪ ለደሀው ኢትዮጵያዊ ስቃይና መከራ ብቻ ነው ያተረፈለት። በሀይማኖት ወይም በጎሳ (በብሔር) "ከፋፍለህ ግዛው" የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት "ከፋፍለህ ግዛን" እንዲህ በማለት ይገልጠዋል፡፡

"Divide and rule (or divide and conquer) in politics and sociology is gaining and maintaining power by breaking up larger concentrations of power into pieces that individually have less power than the one implementing the strategy".

በዚህ ክፍለ ዘመን "ከፋፍለህ ግዛ" ሥርዓት የታየው ሩዋንዳ፣ ሕንድ፣ ናይጄሪያ እና ዩጎዝላቪያ ሌሎችም ቦታዎች በብሔር (በጎሳ) ሲናቆሩ የኖሩ መሆኑን የታወቀ ነው፡፡ በዘር አንዱ ጎሳ የበላይ በማድረግ (ወይም በቤተሰባዊ ውህደት) ሰላምን የሚያስከብር በመምሰል (Colonial power as peacekeeper) የሚመራ ነው፡፡

በሕንድ "በሀይማኖት ከፋፍለህ ግዛ"፤ ይህም ማለት የእስልምና ሃይማኖት እና የሕንድ ሃይማኖት ከተባበሩ ዓለምን ይገዛሉ በሚል ፍርሃት እንዲከፋፈሉ እና እንዲጠላሉ መደረጋቸው የሚታወቅ ነው፡፡ "ከፋፍለህ ግዛ" ዓላማ = ለኢትዮጵያ ለማበጣበጫ ዋና መሳሪያ በመሆን በቀላሉ የማይፈታ የሚቀጥሉት ዘመናት የመከፋፈያ ሥራ ተሰንቅሮባታል፡፡

- 1ኛ) የጎሳን የጥንት ባህሉን በማጋነን ተጨቁናችሁ ነበር በማለት ወይም ከመጨቆን ነጻ አወጣንህ በሚል ፕሮፓጋንዳ ባህሉን ለየት አድርጎ እንዲያከብር ማድረግ፡፡

- 2ኛ) የጥላቻን ሐውልት በመትከል፣ ዘረኝነትን በመካከል መፍጠር (ለምሳሌ አማራን እና ኦሮሞን ለማጋጨት የተቆረጠ ጡት ምስል አኖሌ በሚባል ቦታ የአማራ ንጉሥ የፈጀቸው በማለት ሐውልት ማቆም):: ዘርን ያነጣጠረ የጥላቻ ስብከት ለ 27 ዓመት ሲሰበክም ኖሮአል[2]፡፡
- 3ኛ) በትምህርት ቤት ካሪኩለም ቀርጾ ማስተማር አና ልጆችን አእምሮአቸው እንዲነጥፍ ማድረግ (Brainwash)

የናየጅርያ በዘር መከፋፈል

ናይጅርያ ከብሪታንያ የቅኝ አገዛዝ ነጻ ከወጣች በኋላ ተሰርቶላት የነበረው "በዘር ከፋፍለህ ግዛ" እንድትለያይ ነበር፡፡ እነዚህም ዋናዎቹ ጎሳዎች ሀውሳ፡ ለገቦ፡ እና ዮርባ የሚባሉ ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ እርስ በርስ በከፍተኛ ጠላትነት፤ በመፈራራት፡ በመጠላላት የሚተያዩ ናቸው፡፡ https://www.globalsecurity.org/military/world/nigeria/politics-regional.htm

የናይጀርያው ተወላጅ Rev. Yemi Adedeji, የቸርች ታይመስ ጋዜጣ ላይ የጻፈው ጽሑፍ ወደፊት በምእራባውያን የታቀደ በሚል ያስነብቡናል፡፡ (21 Mar. 2007, It was a start. We await the end')

The divide-and-rule policy, that aimed to create confusion among the African tribes and consequently enslaved them to permanent distrust of each other and the never-ending tribal wars. Or will it be the current exploitation of African natural resources for Western benefit? The list could go on. (https://www.churchtimes.co.uk/articles/2007/23)

ብሩንዲ እና ሩዋንዳ አንድ አይነት ባህል የነበራቸው፡ በጋብቻ የተሳሰሩ ነበሩ፡፡ በብሔር ላይ የተመሠረተ አስተዳደር ስለነበር የእርስ በእርስ ጭፍጨፋ ተፈጸመ፡፡ ወደፊትም ይህ የጥላቻ መንፈስ የሚያሰጋ መሆኑን በአንዳንድ ጽሑፎች ተገልጦ ይታያል፡፡

"በጎሳ ከፋፍለህ ግዛ" የኢጣልያ ፖሊሲ

ከሕወሓት ፖሊሲ ጋር መስማማቱ

በፈረንጆቹ አቆጣጠር 1939 (1933 ዓ.ም.) ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ ለከፋፍለህ ግዛ እንዲመቻት በዘር ላይ የተመሠረተ ሰድስት አስተዳደር በኢትዮጵያ ላይ መሥርታ ነበር፡፡ የአማራ መንግሥት፣ የሐረር መንግሥት፣ የጋላ መንግሥት፣ የሸዋ መንግሥት፣ ኤርትራና ሱማሌ መንግስት፤ በማለት በበላይ ባለሥልጣኑ በኢጣልያ መንግሥት፤ ለንጉሥ ቪክቶር አማኑኤል ስር የሚተዳደር በማለት ካርታ አዘጋጅታ ነበር፡፡

በዘር "ከፋፍለህ ግዛ" ዋና ዓላማ የአንድነትን ኃይል መቀነስ፤ አንድ አድርገው የሚመሩትን መሪዎች፤ አንድ የሚያደርገውን ቋንቋ ወይም ሃይማኖት እንዲጠፉ ማድረግ፡፡ በዘር መከፋፈል ከዚያም (የቁቤን ቋንቋ መፍጠር) ይህ በጣልያን የታቀደው እቅድ በሕወሓት ዘመን ተሳክቶል፡፡

በዙዎች በጦርነቱ የተዋደቁት ደማቸውን ያፈሰሱት ኢትዮጵያውያን አባቶች "ከፋፍለህ ግዛ" የሚለው የቅኝ ገዢዎች ፖሊሲን በመቃወም ኢትዮጵያውያን አባቶች አደዋ ከዚያም ማይጨው ድረስ ሄደው ደማቸውን አፍሰዋል፡፡

ሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ **(**ሕወሓት**)**

ይህ በኢጣልያ የታቀደው የሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ዘመን በተግባር ላይ ዋለ፡፡ ኢትዮጵያውያን በጎሳና በሃይማኖት ሊከፋፍሉ የመጡትን አውሮፓውያንን ያሳፈረች አገር ነበረች፡፡ አሁን ግን ሕወሓት ተበቀለላት ማለት ይቻላል፡፡

ምእራባውያን "ለከፋፍለህ ግዛ" መጠቀሚያ ያደረጓቸው ሕወሓት (ትግራይ ነጻ አውጪ) በሚል ስም ራስን በመጥራት የኢትዮጵያ የመሪነት ወንበር በመያዝ የከፋፍለህ ግዛ መመሪያ ይዞ ኢሕአዴግ በሚል ስም ተሸፈነ፡፡

ዓላማውና ሥራው፤ በይበልጥ አማራን እና ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ማጥፋት ፖሊሲ የመጀመሪያ ከሚባሉት የነበረ ነው፡፡

ትግራይ ነጻ የሚወጣው የሚባለው ከኢትዮጵያ ወይም ከአማራ መሆኑን የሚታወቅ ነው፡፡ በአመራሩ አስተሳሰብ አማራ ማለት በ 5 ይከፈላል....ይላሉ፤ በተለይ ግን አማራ ማለት ኢትዮጵያን ማለትም እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

ይህ ከላይ የምናየው ማንፌስቶ ከ 1968 ዓ.ም. መመሪያ የታገሉበት ዋና ዓላማ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ከሕወሓት ፖለቲከኛ አንደበት ኢትዮጵያዊነት የሚል ቃል በጣም የሚፈራ ሆኖ ለ 27 ዓመት ይኖር ነበር፤ ለዚህም ነፃ አውጭ ነኝ የሚለው ወያኔ ኢትዮጵያዊ ነን እንደማይል መሆኑን ራሳቸው የትግራይ ምስክር ልጆች ናቸው፡፡[3]

ኢትዮጵያውያን ሳይወዱ በግድ የለመዱት የከፋፍለህ ግዛ ቋንቋ

"የኦሮሞ ብሔራዊ ክልላዊ[4] መንግሥት" "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት" "ከትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት" ወይም "የክልሉ መንግስት"፡ "የክልሉ ባንዲራ"[5] "የክልሉ መዝሙር" "የክልሉ ፕሬዘዳንት" "የክልሉ ፖሊስ" "ልዩ የክልሉ ፖሊስ" "የክልል ርዕሰ መስተዳድር" "የክልል ምክር ቤት" "የክልሉ ወሰን" "የክልሉ ካርታ" እና "የክልሉ መታወቂያ"
የሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት)፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያውያን ሳይወዱ በግድ የለመዱት የከፋፍለህ ግዛ ቋንቋ

"የኦሮሞ ብሔራዊ ክልላዊ[4] መንግሥት" "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት" "ከትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት" ወይም "የክልሉ መንግስት"፡ "የክልሉ ባንዲራ"[5] "የክልሉ መዝሙር" "የክልሉ ፕሬዘዳንት" "የክልሉ ፖሊስ" "ልዩ የክልሉ ፖሊስ" "የክልል ርዕሰ መስተዳድር" "የክልል ምክር ቤት" "የክልሉ ወሰን" "የክልሉ ካርታ" እና "የክልሉ መታወቂያ" የሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት)፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢሕዴን)፤ የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ)፤ የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን)፤ የአፋር አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አርዱፍ) ወዘተ…

"የከፋፍለህ ግዛ" ሕገ መንግሥት

1ኛ) የተቀረጸው ሕገ መንግሥት ዘርን እና ቋንቋን መሠረት በማድረጉ አላማው ሉዐላዊ የሆነች ኢትዮጵያን ማፈራረስ፡፡
2ኛ) ሕገ መንግሥት "የኢትዮጵያ ሕዝብ"፣ ከማለት ይልቅ፣ እንደ ዓለም ሕዝቦች ወይም የዓፍሪካ ሕዝቦች እንደሚባለው "የኢትዮጵያ ሕዝቦች" ብሎ "ሕገ መንግሥቱን" ተዘጋጀ፡፡ በኅብረት እንደ አንድ ይታይ የነበረውን ሕዝብ ወደ ልዩነት እንዲመጣ ያደረገው "ሕገ መንግሥቱ" ነው፡፡

3ኛ) …"ሕገ መንግሥቱ" ልዩነት ላይ መሠረት ያደረገ፣ የኢትዮጵያን የቀደመ ታሪክ ያላገናዘበና በኅብረት የማያምን፡፡ ለአንድነት ቅድሚያ የማይሰጥ የመጀመርያው ችግር ነው፡፡ https://www.ethiopianreporter.com/article/5614
4ኛ) "ሕገ መንግሥቱ" ፈረንጅ አዘጋጅቶ የተሰጠ ኢትዮጵያዊነት በውስጡ የሌለ እና በኢትዮጵያ አገር በቀል ዕውቀት መሠረት የሌለው ነው፡፡

5ኛ) አንዱ ከሌላው የሚለይበት ሰንደቅ ዓላማ አዘጋጅቶ መለየቱን መንገር፡፡

6ኛ) ኢትዮጵያውያንን በመታወቂያቸው ላይ እያስገደዱ ብሔራቸውን ሲያስሞሉ ሕዝቡ እንደ ሩዋንዳ ወይም እንደ ደቡብ ሱዳን ያለ የከፋ ችግር ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ነበር፡፡

ለመሳሌ ትዳር ይዞና ቤተሰብ መሥርቶ ከኖረበት ከተማ የሌላ ዜጎች ናችሁ በመባል ከሶማሌ ክልል መታወቂያቸው እየታየ ዕድሜ ዘመናቸውን ያፈሩት ንብረት በሙሉ በማውደም ከመኖሪያቸው ከ700ሺ በላይ ዜጎች ተፈናቅለዋል፡፡ ሉዐላዊ የሆነች አገር ሶማሌ ግዛት እያለች፤ የኢትዮጵያን ድንበር ለማስከበር በሚልዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች (አባት ጡረተኞች ሳይቀር) ደማቸውን ያፈሰሱባት አገር የሐረር ጠቅላይ ግዛት በዘር ላይ በመመሥረት "የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት" ተባለች፤ ይህም የወደፊት አንዱ የቤት ሥራ ነው፡፡

(7ኛ) "እስከ መገንጠል ድረስ" "የራስን ዕድል በራስ ወሳኝ" የሚለው አንቀጽ 39 በተግባር ለመተርጎም ተንኮልን የወደፊቱ የሚያታግል አንዱ ሴራ ነው፡፡

ወያኔ ለ27 ዓመት በብሔሩ ዲክታተርነት ያሸማቀቀበት ቃል

ታሪክን የሚያነሳ ናፋቂ፡ ነፍጠኛ፡ አናሳ ጎሳ፡…ሞራልን የሚነኩ ማሸማቀቂያ ቃላት፡፡

ጉምሩክ ቀረጥ፡ ኤርፖርት ወዘተ… ቋንቋ ተናጋሪ ወይም መጠሪያ ስሙ ቤተሰባዊ ከሆነ ቅድምያ መስጠት፡፡

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የአዲስ አበባ ክልሉ ፊንፊኔ የኦሮሞ ነው በማለት አማራና ኦሮሞን እንዲጠላላ ማድረግ፡፡

"ጽንፈኞች" "ነጠኞች" (ዘረኞች) በጥላቻ መንፈስ ብቅ እንዲሉ ማድረግ፡፡

"እኔ ኢትዮጵያዊነኝ" እንዳይል፤ የኢትዮጵያ ከማለት ይልቅ "የክልሉ መንግሥት ታሪክ" የኔ ብቻ ነው እንዲል (የአክሱም ሐውልት ለወላይታ ምኑ ነው እንዳለው)፤ የናንተ አይደለም የራሴ ነው እያለ እንዲያወድስ)፡፡ አማራ ጎንደር የፋሲል ሕንፃ የአማራ ነው እንዲል፡፡ ….
በኢትዮጵያዊነቱ እንዲያፍር እንዲሸማቀቅ ("ኢትዮጵያ ማለት የመቶ ዓመት ታሪክ ነው" እንዳሉት…) ዝቅ ማድረግ ወዘተ…

በሀይማኖት መከፋፈል (ኦርቶዶክስን እና አማራን አከርካሪውን መምታት … እንዳሉት)፡፡

በአገሪቱ ያሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ማሸማቀቅ፤ እነዚያንም በመካከላቸውም እንዳይግባቡ እርስ በራሳቸው እንዲቃረኑ የቤት ሥራ መስጠት፡፡
ታላቋ ኢትዮጵያን በላቲን ፊደል መክፈል፡፡ ይህ ፕሮግራም የተዘጋጀው በኢጣልያኖች ነበር (Martin Moreno)፡፡

አብሮ የኖረን መለያየትን የማይፈልግ በጋብቻ ተዋሕዶ የኖረንና የተዋለደን ሕዝብ እንዲጠራጠር ማድረግ ፡፡

ቤተሰቦች ልጆች በዚህ የከፋፍለህ ግዛ ሰይጣናዊ መንፈስ መሰቃየት፡፡

በጋብቻም እንዳይገናኙ ማድረግ፡፡ (ሌላም….)

በኢትዮጵያ ታሪክ ከኦሮሞ ጎሳ ያልተዋለደ፡ ከአማራ ጎሳ ያልተዋደ፤ ከትግራይ ያልተዋለደ የለም[6]፡፡ በይበልጥ በአሁኑ ዘመን ከመቼውም በበለጠ ሁኔታ በጋብቻ ተሳስሮአል፤ ተዋልዶአል፡፡ 70 ፐርሰንት ይደረሳል ተብሎ የሚገመተው የኢትዮጵያ ወጣት ከነዚህ ድብልቅ ጎሳ ውጥንቅጥ (ሰርገኛ ጤፍ) ሆኖ ተፈጥሮአል፡፡ ይህም ትውልድ የሚፈልገው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊ ነኝ አንድ ሕዝብ ማለትን ነው፡፡ አንተ ትግሬ (ገንጣይ ነህ)፡ አንተ ኦሮሞ (ዘረኛ ነህ)፡ አንተ አማራ (ነፍጠኛ ነህ) ወዘተ… መባባልን ወጣቱ ትውልድ አይፈልግም፡፡ ነገር ግን አገዛዙ በከፋፍለህ ግዛ መንፈስ አንድ እንዳይሆን የማይፈታ የቤት ሥራን ለሕዝብ ሰጥቶታል፡፡ (የተወሰኑትም በከፋፍለህ ግዛ በማመን አእምሮአቸው ንቡዝ ሆኖአል brainwashed)፡፡

አዲሱ መሪ ጠቅላይ ሚኒስተር ዐቢይ አሕመድ

አገር ወዳድ ምሁራንን "በሽብርተኝነትን" ውንጀላ ወያኔ በግፍ ያሰራቸውን፣ በአሰቃቂ ሁኔታ የተሰቃዩትን አስፈቱ፡፡

"ግንቡ ይፍረስ ድልድዩ ይገንባ" በሚል ለ 27 ዓመታት የተለያዩትን የቤተ ክርስቲያን አባቶች አስታረቁ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ

ሠንደቅ ዓላማ የሕወሓት ምልክት የሆነው ኮከቡ ይወገድ እና ሕዝብ የተስማማበት ይሁን፡፡

"በልበ ወለድ መጽሐፍ የቡርቃ ዝምታ" መነሻ ለኦሮሚያ የቆመው የግጭት ሐውልት ለከፋፍለህ ግዛ እንዲያመች ለማበጣበጥ የተደረገ ስለሆነ ይፍረስ፡፡ "በልበ ወለድ መጽሐፍ የቡርቃ ዝምታ" ይወገዝ፡፡

አንቀጽ 39 ይፋቅልን፡፡

ፌዴራሊየዚም ሥርዓት በጎሳ መሆኑ ቀርቶ በጠቅላይ ግዛት ቢሆን፡፡

የአንድ ጎሳ የበላይነት እና ከፋፍለህ ግዛ ዓላማ ኢትዮጵያዊነትን መንፈስ የሚሸረሽሩ ሁሉ ይለወጡ፡፡

ተግራይ ነጻ አውጭ (የሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት)) የሚለው የትግራይ ሕዝብ መለያ ከ 1968 ዓ.ም. ማንፌስቶ የሚያሳፍር የመለያያ ስም በይቅርታ ይሰርዙ፡፡

ነጻ አውጪ የሚሉት ከኢትዮጵያ ስለሆነ ይህም እንደ ስድብ ስለምንቆጥረው ስማቸውን ይለውጡልን፤

ሕገ መንግሥት "የኢትዮጵያ ሕዝቦች" ከማለት ይልቅ፣ "የኢትዮጵያ ሕዝብ" ተብሎ እንዲጠራ፡፡

"ሕገ መንግሥቱ" ልዩነት ላይ መሠረት ያደረገ፣ በኅብረት የማያምን፡፡ ለአንድነት ቅድሚያ የማይሰጥ "ሕገ መንግሥት" መኖሩ የመጀመርያው ችግር ስለሆነ እንደገና ጥናት ይደረግበት፡፡

ኢትዮጵያን እግዚአብሔር ይባርክ!

ከፋፍለህ ግዛን እድሜውን አሳጥሮ በተዋሕዶ ያኑረን!

አሜን! እንበል፡፡

[1](ናትናኤል መኰንን በፌስ ቡኩ ያወጣው ዘገባ)

[2] How Ethiopian scholars years back questioned Meles Zenawi's highly divisive policies.

https://www.youtube.com/watch?v=sz3M9jiwx0w

Ethiopia: Is he a fortune teller? AAU professor speech now and past
https://www.youtube.com/watch?v=kMv0dNF0Tlk

[3] መታየት የሚገባው https://ethsat.com/2017/12/esat-hr-discussion-tplfs-recent-self-reform-meeting-part-2-16-dec-2017/ በተጨማሪ የአቶ ገብረ መድኅን አርአያን ጽሑፍ ለዚህ ለጥናት የሚረዱ መረጃዎች ናቸው፡፡

[4] ክልል ማለት በአማርኛው አነጋገር ግንብ ወይም መጋረጃ ሲሆን ፤ ለሁለት መቆረጥ፡ መከፈል፡ መሰንጠቅ ከእንግሊዘኛው ጋር በተመሳሳይ Divide ይሆናል፡፡

[5] On Record: When Meles vilified the Flag https://www.youtube.com/watch?v=Px4JQkUvX_Y

[6] አንድነት ጉባኤ ቪዲዮ https://www.youtube.com/watch?v=1szs9dKVZiU

ንቅናቄ (ደኢሕዴን)፤ የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ)፤ የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን)፤ የአፋር አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አርዱፍ) ወዘተ…